# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፦** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 8 ቀን 2003 ዓ.ም.**

**የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች እየታፈሱ መሆኑ ታወቀ፤**

**የወያኔ ፕሮፖጋንዳ ማሳሳቻ ነው ተባለ**

የወያኔ ቡድን የሀገሪቱን ዜጎች በአዲስ መልክ እያፈሰ ወደ እስር ቤት እያጎረ ባለበት በዚህ ወቅት ሰሞኑን ደግሞ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎችን እየመነጠረ ለእስር እየዳረጋቸው እንደሚገኝ ተጋለጠ::

ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች የደረሰን ጥቆማ እንዳስረዳው ከሆነ ከሚያዚያ 3 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ተማሪዎቹን ከየመኝታ ክፍላቸው በምሽት ድንገት ሳያስቡት እየለቀመ ለእስር እየዳረጋቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ወደየት እንደሚወስዳቸው ባለመታወቁ ቤተሰቦቻቸው ለከፍተኛ ጭንቀት መዳረጋቸው ታውቆዋል::

መጋቢት 28 ቀን 2003 ዓ.ም በቲፒ ዩኒቨርስቲ ውስጥ በተከሰተ ብጥብጥ በፌዴራል ፖሊስ አራት ተማሪዎች ከተገደሉና በርካቶች ከባድ ጉዳት ከደረሰባቸው በሁዋላ በተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ

የሚገኙ ተማሪዎች ተቃውሞ በማሰማታቸው የተነሳ ከተኙበት እየታፈሱ እየተወሰዱ መሆኑ ታውቆዋል::

ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፥ከቲፒ፥ከዲላ፥ ከአዳማ፥ከጅማ እና ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ እየታፈሱ የሚጋዙት ተማሪዎች ወደየት እንደሚወሰዱ ያልታወቀ ሲሆን እስከ አሁን ድረስ የታሰሩት በሺህዎች እንደሚቆጠሩ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

የህዝቡን ድጋፍ አገኝበታለሁ ብሎ የአባይ ግድብ ዋነኛ የወያኔ የትኩረት አቅጣጫና ማስቀየሻ ሆኖ እየተወተወተ ባለበት በዚህ ወቅት የኦሮሞ ተወላጅ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የምንጠራ ዘመቻ እያደረገ መገኘቱ በወያኔ ቡድን ውስጥ ሰርፆ የገባ አንድ ታላቅ ችግር መኖሩን ያመላክታል ተብሎዋል::

ሰሞኑን የተጀመረው ይሄው የተማሪዎች ምንጠራ ከቲፒ ዩኒቨርስቲ ተጀምሮ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲን አዳርሶ ወደ ሌሎችም የተዛመተ ሲሆን ብዙዎቹ በፍርሀት ትምህርታቸውን አቁዋርጠው እስከ መሸሽ መድረሳቸው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል::

መላ የሀገሪቱን ህዝቦች በብሔር እና በጎሳ እያበጣበጠ ለ20 ዓመታት የስልጣን ዘመኑን እየገፋ ባለበት በዚህ ግዜ የአንድ ብሔር ተወላጅ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ብቻ ያነጣጠረ የጥቃት በትር መሰንዘሩ ግራ እያጋባም ይገኛል::

በቲፒ ዩኒቨርስቲ የተጀመረው ብጥብጥ ውስጥ ውስጡን ስር እየሰደደ በማደጉ ችግሩ ያልተፈታ ከመሆኑም በላይ የወያኔ ካድሬ መምህራን ችግሩ እንዲባባስ ቤንዚን እያርከፈከፉ ተማሪዎቹ በሰፈር እና በጎጥ ተቡዋድነው እርስ በርስ እንዲደባደቡ በማድረጋቸው የተነሳ ባደረባቸው ፍርሀት  እስከ ዛሬ ድረስ ትምህርት ሊጀምሩ እንዳልቻለ ሲታወቅ በአዲስ አበባና በሌሎቹም ዩኒቨርስቲ ውስጥ ተመሳሳይ የትምህርት መቋዋረጥ እንዳጋጠመ ከደረሰን  ዘገባ ለመረዳት ተችሎዋል::

በፌዴራል ፖሊስ የተገደሉት ተማሪዎች አስከሬን በአግባቡ ለቤተሰቦቻቸው ሳይሰጥ ይልቁንም ቤተሰቦቻቸው አስከሬኑን ለመውሰድ ሲመጡ ሙዋቾች የአመፅ ቀስቃሽ እንደነበሩ እመኑና ፈርሙ ተብለው በግዴታ እንዲፈርሙ መደረጉ የወያኔን ስርዓት ግፈኛነት እና ከናዚ የበለጠ አውሬ መሆኑን ያጋለጠ ነው ሲሉ ሁኔታውን ሲከታተሉ የነበሩ ተማሪዎች  እያነቡ ገልፀዋል::

በአሁኑ ሰዓት የወያኔ ቡድን ሀገር ውስጥ በዜጎች ላይ እየፈፀመ ያለው ግፍና መከራ እንዳይጋለጥ የአባይ ግድብን ሽፋን አድርጎ ተማሪዎችን እየገደለና እየለቀመ ብሎም እያሳደደ በመገኘቱ ቁጥራቸው የበዛ  ተማሪዎች በተፈጠረው ሁኔታ ደንግጠው ትምህርታቸውን እያቁዋረጡ መሆኑም ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እያለ የፖለቲካ ውጥረቱን ለማርገብ ሲል በአንድ ሳምንት ግዜ ውስጥ ድንገት የአባይን ግድብ እሰራለሁ ብሎ የተነሳው የወያኔ ቡድን በህዝቡ ላይ ከዚህ በፊት ከሚፈፅመው በላይ አሁንም ከፍተኛ በደል እየፈፀመ ይገኛል::

ህዝቡ የኑሮ ውድነቱ አይሎ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት ወያኔ የተበላሸ ፖለቲካውን ለመጠገን ሲል ብቻ የአባይ ግድብን እንደ ሽፋን እየተጠቀመበት መሆኑ ታውቆዋል፡፡

እራሳቸው ሾመው ጎጆ ያወጡትን በአምንባገነኑ ግለሰብ የሚመራውን ሻዕቢያ ከስልጣን እናስወግዳለን በሚል ሰፊ ሽፋን ሰጥተው ህዝቡ እንዲከተላቸው ለማድረግና የፖለቲካ ግለቱን ለማብረጃነት ሊጠቀሙበት ቢሞክሩም ውጤታማ ያልሆኑት እነዚሁ የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ሰሞኑን ደግሞ ሌላ ስልት ቀይሰው አዲስ የመነጋገሪያ ርዕስ እንዲቀየር እየሰሩ መሆኑ ታውቆዋል፡፡ ዜጎችን በየእስር ቤቱ እያጎሩ...... የኑሮው ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት እያሻቀበ .....በሁለት ቀን አንዴ ብቻ ቀምሶ ህይወቱን እያቆየ ላለ ዜጋ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ የህይወት አድን መፍትሄ ተነፍጎት  በመርዝ የተለወሰ ማር እንዲመገብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ሌሎችም ከፍተኛ ባለስልጣናት የሻዕቢያ ቡድንን የሚፋለሙ ኃይሎችን በትጥቅም ሆነ በገንዘብ ከመደገፍ አልፎ ከስልጣኑ እናስወግዳለን በማለት ሰፊ ቅስቀሳ ቢያደርጉም መላ የሀገሪቱ ህዝብ ሊከተል ቀርቶ መስማት በመጥላቱ የተበሳጩት እነዚሁ ወገኖች የህዝቡን የትኩረት አቅጣጫ ለማስለወጥ ይሆናል በሚል የአባይ ግድብ መጀመርና ከግብፅ ጋር አዲስ ግብግብ ውስጥ መግባታቸውን ለፕሮፓጋንዳ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፡፡

እንደ ቀልድ ግዜ ይገዛልናል ብለው ያለ በቂ ጥናት በሱዳን ድንበር አቅራቢያ በወያኔ የከልል አከፋፈል የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እየተባለ በሚጠራው ውስጥ ተጀመረ የተባለው ይሄው የአባይ ግድብ ፕሮጀክት በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ  በኑሮ ውድነቱ ላይ ተጨማሪ ሌላ የራስ ምታት መፍጠሩን ህዝቡ በምሬት እየገለፀ ይገኛል፡፡

ምንም እንኳዋን የአባይ ግድብ ቢስራ በመላ የሀገሪቱ ህዝቦች ዘንድ ፍላጎቱ ቢኖርም አቅምን ያላገናዘበ...... የወቅቱ ሁኔታን ከግምት ውስጥ ያላስገባ....... ለግዜያዊ የፖለቲካ ችግር መፍቻ ብቻ ተደርጎ መቅረቡ በህዝቡ ላይ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም በላይ አደገኛ ሁኔታዎች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ከወዲሁ ስጋት እያሳደረ መጥቶዋል፡፡

ዛሬ በሚሊየን የሚቆጠሩ የሀገሪቱ ዜጎች የዕለት ጉርስ መቅመስ ተስኖዋቸው በየሰፈሩ መንገድ ላይ እየወደቁ የሚያነሳቸው እያጡ በዚያው እያሸለቡ ባለበት ሰዓት ፍፁም የሀገሪቱን ተጨባጭ እውነታ ባላገናዘበ ሁኔታ ለራሳቸው ፖለቲካ ሽፋን እና የስልጣን እድሜ ለማራዘም ሲባል ብቻ ቅስቀሳ መጀመራቸው አልፎ ተርፎ የጀመሩትን የፖለቲካ ጨዋታ  የማይደግፍና የሚቃወም ቢኖር እስከ መግደል ደረጃ ድረስ እየተጉዋዙ መሆኑም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በተለያዩ ከተማ ውስጥ የግዳጅ ሰልፎች ህዝቡ እንዲወጣ ከመደረጉም በላይ ህዝቡ ሳይወያይበትና ሳይመክርበት የገንዘብ መጠኑን እራሳቸው የወያኔ ካድሬዎች ተምነው በማዋጣት ተስማማ በማለት እየለፈፉ መገኘቱ ያበሳጫቸው ዜጎች በይፋ እየተቃወሙ በመምጣታቸው ከእስር እስከ መሰወር እየደረሰባቸው መሆኑ ተጠቁሞዋል፡፡

ዓላማው ለርካሽ የፖለቲካ ጥቅም ሳይውል  ሀገርን ለማልማት..... ሀገርን ማሳደግ ቢሆን ኖሮ መጀመሪያ ከስር ጀምሮ ሀብታም ደሀ ሳይባል ህዝቡን ማወያየት ሲገባ የአምባገነን ስርዓቶች

እየተንኮታኮቱ እና እየወደቁ በመጡበት በአሁኑ ወቅት በድንጋጤ እና በፍርሀት እድሜ ለማራዘም ብሎም ከተጠያቂነት ለማምለጥ ሲባል ብቻ ያለ አንዳች ቅድመ ዝግጅት የአባይ ግድብ ተጀመረ መባሉ የሚያሳዝን መሆኑን ህዝቡ በቁጭት እየገለፀ ይገኛል።

ለዚሁ ፕሮፓጋንዳ ይረዳቸው ዘንድ ሰሞኑን በሚዲያ ሰፊ ሽፋን እየሰጡ ሲሆን በወያኔ ስርዓት ከፍተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ግለሰቦችን እያቀረቡ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር ድጋፍ ማድረግ መጀመራቸውንና የቦንድ ግዥ እያደረጉ መሆኑን ህዝቡን ጭምር ለማታለል ሙከራ ቢያደርጉም እውነታው ግን ይህ እንዳልሆነና ውጤቱም የተገላቢጦሽ እንደሚሆን እየተናገሩ ይገኛል።

ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት ክልክል ነው ብሎ ግንቦት 8 ቀን 1997ዓ.ም ጀምሮ ተግባር ላይ ያዋለው የወያኔ ቡድን ለራሱ ፖለቲካ መጠቀሚያ ለማድረግ ባዘጋጀው በዚህ ፕሮፓጋንዳ በክልል ከተሞች ውስጥ ህዝቡን በግዴታ የድጋፍ ሰልፍ እንዲወጣ እያደረገ ይገኛል።

ስትመረቁ ስራ አታገኙም እየተባሉ የሚገኙትን በተለያዩ ዩኒቨርስቲ የሚማሩትን ተማሪዎች በግዴታ ሰላማዊ ሰልፍ እንዲወጡና ህዝቡን መቀስቀሻ እንዲሆኑ ከመደረጉም በተጨማሪ ምንም አይነት ውይይት ሳያደርጉበት ወትሮም ምግብ እያነሰ ከቤተሰቦቻቸው ስንቅ እየተቁዋጠረላቸው ከሚማሩት ከእነዚሁ ተማሪዎች ላይ ለግድቡ መስሪያ ከቀለባቸው ላይ እንዲነሳ ተወሰነ መባሉ አስገራሚና አሳፋሪ ቀልድ መሆኑን እነዚሁ ድራማውን የሚከታተሉ ተማሪዎች እየገለፁ ይገኛሉ።

በፌዴራል ፖሊስ እና በክልል ፈጥኖ ደራሾች ዙሪያቸውን በመትረየስ ተከብበው የድጋፍ ሰልፍ በግዴታ እንዲወጡ የሚደረጉት ተማሪዎች በሚሰራባቸው ሸፍጥ የተነሳ በግቢያቸው ውስጥ ጥያቄ ማቅረብ መጀራቸው እየተነገረ ይገኛል።

እንደ ሌሎቹ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን የድጋፍ ሰልፍ አድርጉ ተብለው ቅስቀሳ ቢደረግላቸውም እራሱ እንዳቦካው እራሱ ይጋግረው እንጂ ህዝብ ባልመከረበት እና ባላወቀበት ሁኔታ እኛ የወያኔን ፖለቲካ አድማቂ አይደለንም በማለት የተቃውሞ ሀሳብ በማቅረባቸው በመደናገጥ በአዳራሽ ውስጥ ስብሰባ እንደገና ቢጠራም ጥቂት የስርዓቱ ተጠቃሚዎች ብቻ ሲገኙ ሌሎች እንዳልተገኙ ለማወቅ ተችሎዋል።

ሁሉን እኔ አውቃለሁ የሚለው የወያኔ ዘረኛና አምባገነን ቡድን የአባይን ግድብ እገነባለሁ ብሎ የህዝቡ ትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ከመሞከርና በዚህም ድጋፍ ለማግኘት ከማሰብ ይልቅ በሀገሪቱ ውስጥ የተንሰራፋውን የረሀብና ችግር ብሎም እርዛት አልፎ ተርፎ የኑሮ ውድነት ለመቅረፍ ቢሞክር የተሻለ ነበር ያሉት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች ወያኔ እንደጮኸለት እና በፕሮፓጋንዳ እንዳደመቀው እንደማይሆን በጥቂት ግዜ እንደሚታይ እየገለፁ ይገኛሉ።

የአባይን ግድብ እንሰራለን ብሎ ጡሩንባ ከመነፋቱ አስቀድሞ አምስት አመቱን የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ተግባራዊ ለማድረግ በውጭ ሀገር የሚገኙ ዲያስፖራዎችን ለማነጋገር አስቀድሞ ፕሮግራም በተያዘው መሰረት የተለያዩ ሀገሮች ዋና ዋና የተባሉት ነባር ካድሬዎች ቢሄዱም አጥጋቢ ምላሽ ከማጣታቸውም በተጨማሪ ከፍተኛ ተቃውሞ እንደገጠማቸውና ውርደት እንደተከናነቡ ከተለያዩ ቦታዎች የደረሱን ጥቆማዎች አስረድተዋል።

አዙሮ ማሰቢያ የሌላቸው .......ጥቅማቸውን እንጂ የኢትዮጵያን ህዝብ የረሱ...... ዜጎች በወያኔ የግፍ በትር እየተወቀጡ መሆኑን እያወቁ ዲሞክራሲ ሰፍኖዋል እያሉ ፕሮፓጋንዳ የሚነዙ.....በሚሊዮን የሚቆጠሩ የሀገሪቱ ዜጎች በርሀብ እንደ ቅጠል ሲረግፉ ደልቶዋቸው ነው የሚሉ ......አድር ባይ ሆድ አደሮች የተሰባሰቡበት የዚሁ ስብሰባ ውጤት ድምሩ ዜሮ በመሆኑ መጨረሻውም ባዶ መሆኑ አይቀሬ ነው ተብሎዋል፡፡

የተደረገው የደመወዝ ጭማሪ ከወቅቱ የኑሮ ውድነት ጋር አይጣጣምም ስለዚህ ድጎማ ይደረግልን እያሉ ጥያቄ እያቀረቡ ያሉት የፌዴራል ፖሊስ አባሎች ባልመከሩበትና ባላወቁበት ሁኔታ ጥቂት አጨብጫቢ መኮንኖች ብቻ በተገኙበት ለግድቡ መስሪያ የሚውል የአንድ ወር ደመወዛችን እንዲቆረጥ ወስነናል ተብሎ በመተላለፉ የተደናገጡ ፖሊሶች አለቆቻቸውን በጥያቄ እያጣደፉ ይገኛሉ፡፡

ዋጋውን አወርዳለሁ...... ገበያውን አረጋጋለሁ..... ብሎ ነጋዴዎችን ከጨዋታ ውጭ ያደረጋቸው ወያኔ የዘይት አቅርቦት በገፍ ነው እያለ ሲለፍፍ የነበረ ቢሆንም ዛሬ አንድ ሊትር ዘይት ከ50 ብር በላይ በጥቁር ገበያ እየተሸጠ መገኘቱ ስርዓቱ እንቁራሪት ሆኖ ዝሆንን ለማከል ከአቅሙ በላይ እየተንጠራራ መሆኑን ያሳያል ሲሉ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እየተሳለቁበት ይገኛል፡፡